# አብዮታዊት ኢትዮጵያ ፲፰




ጥር ፲፭—፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# ለለየለት ፍልሚያ ዝግጅት

ካለፉት ጥቂት ወራት ወዲህ የኢትዮጵያን ሁኔታ ልዩ መልክ የሚሰጠው ነገር የአብዮትና የፀረ አብዮት ኃይሎች እጅግ በጠራ ሁኔታ ሚና መለየታቸውና ለለየለት የመጨረሻ ፍልሚያ በሁለቱም ወገን የሚደረገው መሯሯጥ ነው ።

በንቃቱ በድርጅቱ በትጥቁ ከፍተኛ ድሎችን እየተቀዳጀ የመጣው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስና ነባር ጠላቶቹን ከመጠን በላይ አስበርግጓቸዋል ። ባለፉት ጥቂት ወራት እንኳን የአብዮቱ መግፋት ያገኛቸውን ድሎች ዘወር ብለን ብናያቸው እጅግ ብዙ ናቸው ። በገጠር የነቃውና የተ ደራጀው ገበሬ አድኃርያንን ትጥቅ እያስፈታና ራሱን እያስታጠቀ መሬቱን እጁ ያስገባል። የገዛ ዕድሉ ወሳኝ ሆኖ ፤ የገዛ ምርቱ ባለቤት ሆኖ አዲስ ኑሮ ይገነባል ። በከተማ የኢትዮጵያ ወዝ አደሮች የንቃት ደረጃቸው እንዳይዳብር የኢ.ህ.አ.ፓ. ግልገል ፋሽስቶች የፈጸሙባቸውን ከታሪክ የማይ ፋቅ ወንጀል በሐቀኛ አብዮታውያን ትግል አክሽፈው ዛሬ እንኳን የለየለትን ጠላት ይቅርና መስለው የተደባለቁ የተኰላ ባሕታውያን ለይተው ማወቅና እነሱንም መዋጋት ጀምረዋል ። የኃለ ሥላሴ ፋሽስታዊ መንግሥት ወዝአደሩን በተደራጀ መልክ ለማንበርከክ እንዲችል የጥቂት አድኃሪዎች መፈንጫ የነበረውና ከየካቲትም ወዲህ የነቁ አድኃሪዎች አብዮቱን ለማኮላሸት ሊጠቀሙበት ይሞክሩ የነበረው ኢ. ሠ. አ. ማ. ፈርሶ በሱ መቃብር ላይ በወዝ አደሩ የነቃ ትግል ለትግል የተወለደው አብዮታዊው መ. ኢ. ሠ. ማ. ተቋቋመ ። የለየላቸውን አድኃሪዎች ብቻ ሳይሆን ሠርገው የገቡትን ቡችሎቻቸውን የኢ. ሀ. አ. ፓ. ቅጥረኞች ከመሀል ሠርጎ በማስወጣት በየከተማው የሚገኘው ሰፊ ሕዝብ በያለበት ዲሞክራሲያዊ የሕብረት ሥራ ማኅበራትን አቋቁሟል ። ወጣቶች ሴቶች ፤ መምህራንና ሌሎችም የሕብረተሰብ ክፍሎች በመካከላቸው ያሉትን ፀረ ሕዝቦችና የኢ.ህ.አ.ፓ. ሠርጎ ገቦችን በማጋለጥ እያደጉ በትግል ወደፊት በመግፋት ላይ ናቸው ። በዓለም አቀፍ ደረጃም የነኢ.ህአፓ ኢዱዩ ፀረ ኢትዮጵያ ዘመቻ በአድኃሪ ዓረብ መንግሥታትና በኢምፔሪያሊስቶች ጆሮ ተደማጭነት አገኘ እንጂ የኢትዮጵያን አብዮት ሶሻሊስት አገሮችና የዓለም ተራማጅ ሕዝቦች አውቀውታል ። አቅፈውታል ። ደግፈውታልም ።

ባጭሩ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ ወደፊት ተራምዷል ። በአጭር ጊዜ ውስጥ መጋፈጥ የሚገባውን አድኃሪ ኃይሎች ያለ የሌለ ኃይላቸውን አንቀሳቅሰውና አስተባብረው የሚጭኑበትን ወሳኝ የሆነ ትግል በድል አድራጊነት ለመወጣት አስተማማኝ ሁኔታ አለ ። ነገር ግን የሰፊው ሕዝብ ትግል መራመድና የንቃቱ ፤ የድርጅቱና የትጥቁ መጠናከር በምንም ዓይነት አድኃሪዎች አለቁ ደቀቁ የሚያሰኝን አይደለም ። ወሳኙ ትግል አድኃሪዎችን የሚያደቃቸው ትግል ፤ እንዳልነበሩ አድርጎ የሚደመስሳቸው ትግል ገና ወደፊት ነው ። በአጭር ጊዜ መልኩ ሲታይ አድኃሪዎች ሊጠናከሩ ይችላሉ ።

ለዚህ ምሳሌ ኢ.ህ.አ.ፓ የተባለውን የከሀዲዎች ቡድን የክስረት ሂደት መመልከት ትምህርት ይሰጠናል። ብዙ የዋሆች ፤ ኢ.ህ.አ.ፓ በሕዝቡ ስለተተፋ ያለቀ የደቀቀ የሚመስላቸው ነበሩ። ነገር ግን ይኸ ስህተት ነበር ። ይህ ቡድን በአድኃሪነቱ ፤ በከሀዲነቱ እየተጋለጠ ሲሄድ የዚያኑ ያህል ዱሮ «ተራማጅ ሆነብን» ብለው ያዝ ለቀቅ ያደርጉት የነበሩት እነሲ.አይ.ኤና መሳፍንቱ ያቅፉታል ይደግፉታል ። ስንቅና ገንዘብ ያገሮርፉለታል ። ያስታጥቁታል ። ስለዚህ ከሰፊው ሕዝብ ቢባረርም ከአኃድ



ሪው ሰፈር ለመቃረም ያመቸ ሁኔታ እንደሚፈጥረለት ሌላው ቢቀር ሰሞኑን ኢድዩና ሲ.አይ.ኤ. የተለቀቁበት ኢ.ህ.አ.ፓን የማሞገስ ዘመቻ ምስክር ነው ። ስለሆነም የሕዝቡ ትግል እየገፋ ሲሔድ አዲስና ነባር አድኃርያን ኃይላቸውን አስተባብረው የሚታገሉበት አዲስ ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው ። ሰፊው ሕዝብ በዚህ መልክ ትግሉና ድሉ ለሚፈጥርበት አዲስ የትግል ምዕራፍ መዘጋጀቱን ትቶ ባገኛቸው ድሎች በመሳከር ብቻ ከተዘናጋ አብዮቱን ሊያስቀለብስ ይችላል ።

በሰፊው ሕዝብ ትግል መግፋት የተነሳ የአድኃርያን ትብብር እንደሚጠናከርና የአልሞት ባይ ተጋዳይ መፍጨርጨራቸው ከዱሮው እንደሚጨምር በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በገሀድ የሚካሔደው የተቀነባበረ ሴራ ምስክር ነው ። አብዮታችን ሀቀኛ ይዘቱ ተረጋግጦ፤ እውነተኛ ገጽታው ታውቆ ሶሻሊስት አገሮችና የመላ ዓለም ተራማጆች ስለደገፉት የተጠናከረውን ያህል የዓለም ፀረ አብዮት ኃይሎች ደግሞ የኢትዮጵያን አድኃሪዎች አቅፈውና ደግፈው ተነስተዋል ።

በዚህ መልክ በሀገር ውስጥ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች የአብዮቱ መግፋት ያስተቃቀፋቸውን ያህል በዓለም አቀፍ ደረጃ በርግጥ ተዋውቀው ጐን ለጐን እንዲሰለፉ አድርጓቸዋል ። ስለሆነም ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ በሀገራችን አብዮትና ፀረ አብዮት በየበኩላቸው ኃይላቸውን እየሰበሰቡና እያጠናከሩ ናቸው ። አድኃሪ ኃይሎች ይህ አሁን የሚመክሩት የተቀነባበረ ሴራ የሞት ወይም የሽረታቸው እንደሆነ ይገባቸዋል ። ስለዚህ በድል አድራጊነት ለመወጣት የማይሞክሩት መንገድ የላቸውም ።

በሀገር ውስጥ አድኃሪ ኃይሎች በመሀከላቸው ያሉትን መለስተኛ ልዩነቶች አቻችለው አብዮትን ያህል ጠላት አላቸውና በአንድነት መቆም እንዳለባቸው ተገንዝበው በሚነዙት ፕሮፓጋንዳ በሚያካሂዱት ፀረ ሕዝብ አመጽ ፤ ባላቸው የነሲ.አይ.ኤ ድጋፍ ኢዲዩና ኢ.ህ.አ.ፓ. የአባትና ልጅ ያህል እንጂ ሌላ ምንም ልዩነት እንደሌላቸው ግልፅ ሆኖ እየታየ ነው ። ዓለም አቀፋዊ ትብብሩንም ማየት ብዙ ማፈላለግ አያስፈልግም ። የኢትዮጵያን አብዮት የከበቡት አድኃሪ ኃይሎች ለኢ.ህአፓ ፤ ለኢዲዩና ለኢኤልኤፍ የገንዘብ ፤ የማቴሪያል ፤ የጦር ማሰልጠኛ ሰፈር ፤ የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ ይሰጣሉ ። የኛዎቹ ፀረ አብዮት ኃይሎች ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአካባቢው ፀረ አብዮት ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ የሚካሔዱትን ዘመቻ እያስተጋቡ ድጋፍ ይለግሳሉ ። በተለይ ኢህ.አፓ.ና ኢዲዩ ኢትዮጵያን እንደወራሪ አድርጎ ለማቅረብ ሱዳንና ሱማሊያ ያፋፋሙትን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በግልጽ ማስተጋባት የጀመሩት ዛሬ ሳይሆን ከጥቂት ወራት በፊት እንደሆነ እናውቃለን ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ መቀራረብና መሸጋሸግ ተደርጎ የኢትዮጵያ አብዮት በንቃት ፤ በድርጅትና በትጥቅ ጐዳና ላይ ከመቸውም ይበልጥ ገፍቷል ። በሌላ በኩል ደግሞ አድኃሪ ኃይሎችም በውስጥና በውጭ ኃይላቸውን አስተባብረው ፤ አብዮታችንን በትጥቅ ሊያጠፉት ተነስተዋል ። ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ወደወሳኙ ፍልሚያ በመቃረብ ላይ እንገኛለን ። ጠላቶቻችን ነቅተዋል ፤ ተደራጅተዋል ኃይላቸውን አስተባብረዋል ታጥቀዋል ። የነቃውና የተደራጀውም የሰፊው ሕዝብ ሰፈር ኃይሉን አስተባብሮና ታጥቆ ካልተቋቋማቸው አብዮታችን ላይ የሚያንዣብበው የቀልበሳ ደመና በአድኃርያን አእምሮ ከሚመላለስ ቅዠት መሆን አልፎ ለኢትዮጵያችንና ለአብዮታችን የችሎን የመሰለ እውነት ይሆናል ። ይህንን ሊያድነው የሚችለው ሰፊው ሕዝብ የደረሰበትን የንቃትና የድርጅት ደረጃ አድኃርያን በትጥቅ እንዳይፈቱት ታጥቆ መጠበቅ ብቻ ነው ። አብዮቱን ለመጠበቅ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ሰፊው ሕዝብ መታጠቅ አለበት ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።